*ናንሲ ኤስ ግራዝሚክ*
*የስቴቱ ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ*

*ማርቲን ኦማሊ*
*አገረ ገዢ*

Maryland State Department of Education
Division of Special Education/Early Intervention Services
200 W. Baltimore Street, Baltimore, MD 21201
www.marylandpublicschools.org

# የልዩ ትምህርት ግልግልን በተመለከተ ባብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች የወላጅ መምሪያ

1. **ግልግል ምንድን ነው?**

   ግልግል ማለት አካለስንኩል በሆነ ወይም አካለስንኩልነት አለበት ተብሎ በሚታመንበት ተማሪ ወላጆች እና ለተማሪው ትምህርት ኃላፊ በሆነው የሕዝብ ድርጅት መካከል ያሉ አለመስማማቶችን ለመፍታት በፈቃደኝነት መደረግ የሚችል ሂደት ነው።

2. **ግልግሉን የሚመራው ማነው?**

   ገላጋይ ሆኖ የሚቀርበው ሰው ስለግልግል ስልቶችና ቴክኒኮች ተገቢውን ሥልጠና የወሰደ የሜሪላንድ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ ሠራተኛ ነው።

3. **አለመግባባቱን ለመፍታት በሚሞከርበት ጊዜ ገላጋዩ ምን ዓይነት ሚና አለው?**

   የገላጋዩ ሚና ሰዎች ስምምነት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ነው። ገላጋዩ ገለልተኛና የማንኛውንም ወገን የማይይዝ ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ባብዛኛው የሚስማሙባቸውን ነጥቦች እንዲያገኙና አለመግባባቱን በተመለከተ መፍትሔዎች የሚገኙበትን መንገድ እንዲፈልጉ ይረዳል።

4. **የግልግል ጥያቄ ካቀረብኩ የሕዝብ ድርጅቱ የመሳተፍ ግዴታ አለበት?**

   የለበትም። ግልግል በፈቃደኝነት የሚደረግ ሲሆን፣ የአለመግባባቱ ሁለቱም ወገኖች ግልግል ለመጠቀም መስማማት አለባቸው። የሕዝብ ድርጅቱ ግልግል ለመጠቀም የመስማማት ግዴታ <u>ባይኖርበትም</u>፣ አብዛኛውን ጊዜ ይስማማል።

5. **የሕዝብ ድርጅቱ የግልግል ጥያቄ ቢያቀርብ የመሳተፍ ግዴታ አለብኝ?**

   የለብዎትም። በጥያቄ ቁጥር 4 ላይ እንደተባለው ግልግል በፈቃደኝነት የሚደረግ ነው።

6. **የፍትህ ሂደት አቤቱታ ሳላስገባ የግልግል ጥያቄ ማቅረብ እችላለሁ?**

   አዎን። አለመግባባትን ለመፍታት በማንኛውም ጊዜ የግልግል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። እንደውም አለመግባባትን በተቻለ መጠን በቶሎና የፍትህ ሂደት አቤቱታን ከማስገባት በፊት ለመፍታት መሞከር ይመረጣል።

7. ግልግሉ ላይ ማንን አብሬ ማምጣት እችላለሁ?

አለመግባባቱን ለመፍታት ይረዳል ብለው የሚያምኑትን ማንኛውም ሰው ይዘው መምጣት ይችላሉ። ይህ ማለት ታማኝ ጓደኛ፣ ዘመድ፣ ድጋፍ ሰጪ ወይም ጠበቃን ያካትታል። በነጻ ወይም በአነስተኛ ዋጋ ሕግ-ነክ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰጡ ድርጅቶችን ዝርዝር ለማግኘት የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርም ይመልከቱ ወይም የሜሪላንድ ሲቴት የትምህርት ክፍል፣ የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ዌብሳይትን በ www.marylandpublicschools.org አድራሻ ይጎብኙ (Divisions፣ Special Education Early Intervention መርጠው ከዛ Complaint Investigation and Due Process Branchን ይምረጡ)።

8. የግልግሉ ዋጋ ምን ያክል ነው?

ግልግሉ እርስዎን ወይም የሕዝብ ድርጅቱን ምንም ወጪ አያስወጣዎትም። የግልግሉ ዋጋ የሚከፈለው በስቴቱ ነው።

9. ግልግሉ ተደርጎ ስምምነት ላይ ስንደርስ ምን ይሆናል?

ገላጋዩ እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ የሚፈርሙት ስምምነት ጽፎ ግልባጭ

10. ግልግል ሄደን ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻልን ምን ይሆናል?

ግልግል ላይ ተሳትፈው ከሕዝብ ድርጅቱ ጋር ስምምነት ላይ ካልደረሱ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦ (1) በሌላ ጊዜ ግልግል ለማድረግ እንደገና መሞከር፣ (2) በችሎት መቀጠል (ከመጀመሪያው በቂ የፍትህ ሂድት አቤቱታ አስገብተው ከሆነ)፣ (3) የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስገባት፣ ወይም (4) አለመግባባቱን ለመፍታት ሌላ መንገድ መፈለግ።

የፍትህ ሂደት ችሎት ለማድረግ ከቀጠሉና ገላጋይዎ የአስተዳደር ሕግ ዳኛ ከነበረ፣ ያው ዳኛ ችሎትዎ ላይ አይመደብም።

11. የግልግል ጥያቄ ባስገባሁ በስንተኛው ጊዜ ነው ይከሰታል ብዬ መጠበቅ ይምችለው?

የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ ግልግሉ በተቻለ መጠን በቶሎ እንዲደረግ ቀጠሮ ለማስያዝ ሙከራ ያደርጋል፣ ሆኖም ግልግሉ የፍትህ ሂደት ችሎት የማግኘት መብትዎን አይነካም ወይም አያዘገይብዎትም።

12. በግልግሉ ላይ የተደረሰበትን ስምምነት የሕዝብ ድርጅቱ ካላከበረ ምን ይሆናል?

በጽሑፍ ቀርቦ የተፈረመ የግልግል ስምምነት በሕግ የሚያስገድድና በማንኛውም በአውራጃው መሥራት የሚችል የስቴት ፍርድ ቤት ውስጥ ወይም የፌዴራል አውራጃ ፍርድ ቤት ውስጥ በሕግ መከበር የሚችል ነው።

13. እኔ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ በግልግሉ ላይ የተኪያሄዱ ውይይቶችንና ድርድሮችን ወደፊት የሚደረጉ ሂደቶች ላይ መጠቀም እንችላለን?

አይቻልም። የግልግል ሂደቶች ዝግ ሂደቶች ናቸው። በግልግል ጊዜ የተደረጉ ውይይቶች በምስጢር መያዝ ያለባቸውና ለማንኛውም ተከታይ ችሎት ወይም ማህበራዊ እርምጃ እንደ ማስረጃ ሊጠቀሙባቸው አይቻልም። ግልግሉ ከመጀመሩ

በፊት፣ ወላጆች ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ጉዳዩን በምስጢር መጠበቅ እንደሚገባቸው የሚያረጋግጥ መተማመኛ እንዲፈርሙ ሊጠየቁ ይችላሉ።

14. **የግልግል ጥያቄ የማቀርበው እንዴት ነው?**

***ጥያቄውን ለማቅረብ ከአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ የሚገኘውን የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርምን መጠቀም ይመረጣል። ሆኖም ማንኛውም የሚያስፈልገውን መረጃ ሁሉ የያዘ በጽሑፍ የቀረበ ጥያቄ ሁሉ የግልግል ሂደቱን ሊያስጀምር ይችላል። ፎርሙን ለማግኘት ለልጁ ትምህርት ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ድርጅት ወይም የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ (OAH) ጋር መደወል ወይም መጻፍ ይቻላል። ፎርሙ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ ዌብሳይት ላይ በአድራሻ www.oah.state.md.us እና በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ዌብሳይት ላይ በአድራሻ www.marylandpublicschools.org ይገኛል።***

15. **የግልግል ጥያቄዬን የት ነው የምልከው?**

ጥያቄዎ መላክ ያለበት ለልጁ የትምህርት መርሀ ግብር ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ድርጅት <u>እና</u> ለአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ (OAH) ነው። ፎርሙ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በእጅ ሊሰጥ ይችላል። የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ (OAH) በኢሜል የተላኩ ጥያቄዎችን አይቀበልም፣ አድራሻው 11101 Gilroy Road, Unit E/Clerk's Office, Hunt Valley, MD 21031 ነው የፋክስ ቁጥሩም 410-229-4277 ነው።

16. **ያስገባሁትን የግልግል ጥያቄ መልሼ ማውጣት ብፈልግ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ በጠየቀው ግልግል ላይ ለመሳተፍ ሐሳቤን ብቀይርስ?**

በተቻለ መጠን በቶሎ ለአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ (OAH) እና ለሕዝብ ድርጅቱ ጥያቄዎን መልሰው ማውጣት እንደሚፈልጉ የሚገልጽ የጽሑፍ ደብዳቤ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በእጅ ይስጡ። ደብዳቤው ጥያቄውን ለምን መልሰው እንደሚያወጡ የሚያስረዳ መረጃ ሊይዝ ይችላል።

በድጋሚ፣ ግልግል በፈቃደኝነት የሚደረግ ነው፣ ስለዚህ አንድ አለመግባባትን በግልግል መፍታት እንደማይፈልጉ ከወሰኑ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ በጠየቀው ላይ መሳተፍ ባይፈልጉ፣ የማድረግ ግዴታ የለብዎትም።

17. **ጥያቄዎቼን በሙሉ አልመለሳችሁም። እርዳታ ለማግኘት የት መሄድ እችላለሁ?**

በመጀመሪያ የሕዝብ ድርጅቱ የሰጥዎትን የሥርዓት መከላከያ ሰነድ ይመልከቱ። ለሌሎች ጥያቄዎች መልስ መስጠት የሚችሉት ለልጁ ትምህርት ኃላፊ ከሆነው የሕዝብ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ተገቢ ሠራተኞች፣ ለመሳካት አጋሮች ወይም የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች ማዕከል (Partners for Success or Family Support Services Center)፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች ቢሮ (410-767-0267 ወይም 1-800-535-0182, ext. 0267)፣ ወይም የአስተዳደራዊ ቅሬት ሰሚ ቢሮ ሠራተኛ ቢሮ (410-229-4281)። የልዩ ትምህርት ጉዳዮችን በተመለከተ በነጻ ወይም በአነስተኛ ክፍያ እርዳታ የሚሰጡትን ድርጅቶችንም ማማከር ይችላሉ (የነዚህ ድርጅቶች ዝርዝር *የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ* ፎርም ላይ ተያይዞ ይገኛል)።

*የገንዘብ ድጋፍ የቀረበው በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ከ IDEA ክፍል B ችሮታ #HO27A070035A፣ የዩ ኤስ የትምህርት ክፍል፣ የልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮ በኩል ነው። በዚህ ውስጥ የተገለጹ አስተያየቶች የዩ ኤስ የትምህርት ክፍልን ወይም ማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅትን ወክለው አይደለም እንደሱም መታየት የለባቸውም። የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከልዩ ትምህርት መርሀ ግብሮች ቢሮ፣ ከልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮና ከዩ ኤስ የትምህርት ክፍል ነው። ይህ መረጃ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው እንዲጋሩት ይበረታታሉ*

*ሆኖም ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ አገልግሎቶች መምጣቱን እባክዎን ያስታውቁ።*

*የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጳዕኖ ሊያሳድር የሚችል በጎሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካለ ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የክፍሉን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የእኩልነት ማረጋገጫና መፈጸሚያ ቅርንጫፉን (Equity Assurance and Compliance Branch) በስልክ ቁጥር (410)767-0433 በመደወል ወይም በፋክስ ቁጥር (410)767-0431 መገናኘት ይችላሉ። የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን (Americans with Disabilities Act (ADA)) በደነገገው መሠረት ይህ ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ በአማራጭ አቀራረቦች ዝግጁ ሆኖ ይገኛል። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኘውን የልዩ ትምህርት/ቅድመ ገላጋይ አገልግሎቶችን ክፍል በስልክ ቁጥር (410)767-0858 ወይም በፋክስ (410)333-1571 ይገናኙ።*

Dev. 10/2007